ፓኖራማ ቁጥር 54

የትዝብት አድማስ

ታህሣሥ 3 ቀን 2001 ዓም

# <u>የቆሰለ አራዊት የተከበበ ሠራዊት</u>

በአዳኞች የቆሰለ አውሬና በጠላት የተከበበ ሠራዊት ሁኔታው ባመጣባቸው ጭንቀት ምክንያት ተመሳሳይ ባኅርይ ያሳያሉ፡፡ አውሬው ቁስሉ እየገነገነበት ሲሄድ÷ሠራዊቱ ደግሞ÷ ከበባው የተጠናከረ ሲመጣበት ሁለቱም በአካልና በሥነአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ ስለሚነከሩ ከጭንቀታቸው የተገላገሉ ስለሚመስላቸው÷ ተመሳሳይ ድርጊት ለመፈፀም ይሞክራሉ÷ ይፈራገጣሉ ይፍጨረጨራሉ፡፡ የሞት የሽረት ርምጃ ለመውሰድ ስለሚከጅሉም÷"መሞታችን ላይቀር አጥፍተን እንጥፋ" ከሚል የአልሞት ባይ ተጋዳይ ውሳኔ ከመውሰድ አይቆጠቡም፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ከመጨረሻው የተስፋ መቁረጥ ደረጃ ሲደርሱ ነው፡፡ከመሞታቸው በፊት አስቀድመው ስለሚሞቱ እናጠፋዋለን ያሉትን ከማጥፋታቸው በፊት እነርሱ እራሳቸው ይጠፋሉ፡፡አጠፋፋቸው ደግሞ÷የቆሰለው አውሬ በራሱ ቁስል ብርታት የተነሳ እየተወራጨ÷እየተፈራገጠና አፈር እየጋጠ ሲወድቅ÷የተከበበው ሠራዊት ደግሞ ከፍርሃትና ከጭንቀት የተነሳ÷ፍራቻውና ጥላቻው ተወህደውበት እርሱ በእነርሱ÷ እነርሱ በእርሱ ይጠፋፋሉ፡፡

በቆሰለ አውሬና በተከበበ ሠራዊት ያለው ልዩነት÷ በዚህች ቀላላ ንፅፅር ብቻ ተወስኖ ሊተው የሚገባው እንዳልሆነ ግን መስተዋል ያለበት ክስተት ነው፡፡ የተከበበው ሠራዊት የሰዎች ክምችት እንደመሆኑ÷ በሥነ ፍጥረቱ÷ ከአውሬ ባኅርይና ሥነ-አዕምሮ በእጅጉ ይለያል፡፡ ስለሆነም÷ወታደሮቹ በአለቆቻቸው ላይ ዕምነትና አክብሮት ስለማይኖራቸው÷ የአዛዥና ታዛዥ÷ የሥነሥርዓትና የአንድነት መንፈስም ሆነ የኅብረት አንድነት ይፋለሳል፡፡ መናናቅ÷መፈራረት÷የተስፋ መቁረጥ÷ሁኔታ በስፋት ይከሰታል፡፡የዓላማ መሸርሸር ይስፋፋል÷የክህደት ድርጊት ይፈፀማል፡፡ጠቅላላ የሠራዊቱ መዋቅርና ተቋም ይፋለሳል፡፡ እያንዳንዱ የሠራዊት ክፍል የየራሱን ርምጃ በመሰለው መንገድ ለመውሰድ ይሞክራል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሠራዊት ከሠራዊቱ አዛዦች ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ጠቅላላይ መምሪያው ድረስ ያሉትን የመከላከያ ባለሥልጣናት ውሳኔና ትዕዛዝ ሳይቀበል ይቀርና የራሱን የመጨረሻ ርምጃ ለመውሰድ ወስኖ ለአመች ሁኔታዎች ይዘጋጃል፡፡ ከሞላ ጎደል ሁለት አማራጮች ብቻ ይኖሩታል፡፡ አንደኛው ነጭ ጨርቅ እያውለበለበ÷ከተከበበት ምሽግ በመውጣት÷ እጁን ለባላንጣው ሠራዊት መስጠት ሲሆን፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ወኔው ጨርሶ ካልሞተበት÷ ወታደራዊ ሀሞቱ ካልፈሰሰበትና ሀገራዊ ኩራቱ ካልተሰወረበት÷ በቆራጥነት ምሽጉን ጥሶ በመውጣት ከከበበው ሠራዊት ጋር እየተዋጉ ማምለጥ ወይም ማለቅ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ የጦርነት ታሪክ የሚያስረዳው፥ በአመዛኙ ሁለተኛውን ክስተት ነበር። ከጥቂት መሪዎች በስተቀር!

ከላይ ለመግለፅ የተሞከረው በእንስሳትም ይሁን በሠራዊት ዘንድ የሚደረገው ከበባና ጥቅት የሚያስከትለውን ሁኔታ ቢሆንም፥ በአምባገነን ሥርዓት የሚማቅቁት ሕዝቦች በመጨረሻ በጨቋዮቻቸው ላይ አምርርው ሲነሱ የሚፈጠረው ሀኔታም ተመሳሳይነት ይኖረዋል። መንግሥትና ኅብረትሰብን አስማምቶ ሊያኖራቸው የሚችል፥ ሀገሪቱ፥ በዜጎቿ ፈቃድና ስምምነት መሠረት በሚፀድቀው የሀገሪቱ ህገ መንግሥት ዙሪያ ይሽከረከራል። በዚህ ህገ መንግሥት ተመስርቶ በሚቋቋመው መንግሥትና በዜጎቹ መካከል የሚደረገው የጋራ ስምምነትና ቃልኪዳን የሕዝቡን መብትና ግዴታ፥ የመንግሥትንም ኃላፊነትና ግዴታ፥ እንዲሁም የሥልጣኑን ገደብና ተጠያቂነት፥ሥልጣንና ኃላፊነት በደንብ ተወስኖ ይገለፃል። የአንድ ሀገር ህገ መንግሥት የዚያች ሀገር የበላይ ህግ በመሆኑ፥ መንግሥትም ሆነ ወይም ሌላ  ኀይል ሊጥሰው ፥ ሊለውጠውም ሆነ እንደፈለገ ሊያሽመደምደው አይችልም። ያ ከሆነ ደግሞ፥ ነገር ተበላሸ፥ ሀገር ተረበሸ፥ ሕዝብም አመፀ ሸፈተ ማለት ነው።ሕዝብ አመፀ፥ ጀግና ሸፈተ ማለት ደግሞ፥ ሀገር ሠላም አጣ፤  ሥርዓት አልበኝነት ሰፈነ፥ ሠላማዊ ህይወት ጠፋ ማለት ነው። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ቃል ኪዳኑን አፍርሶ፥ ከሕዝብ ጋር የገባውን ስምምነት ጥሶ የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት የደፈረ፥ዜጎቿንም የናቀ፥ሀገሪቱንም ያዋረደ በመንግሥት ኮርቻ የተፈናጠጠው ክፍል ነው።  ያን ጊዜ ነው ይህ ወንበዴ መንግሥት  በጠላት እንደተከበበ ሠራዊት መግቢያ መውጫ የሚያጣው፥ ይህ በሚመከሰትበት ወቅት፥ ሊመጣ የሚችለው በመጀመሪያ  ደረጃ፥ ውንብድናውን የፈፀሙትን ግለሰቦች፥ዙሪያውን ከብቦ ማስጨነቅና ከወንበራቸው ማንሳት ይሆናል።  ሀገር በመሠረታዊ መልኩ ሠላምና መረጋጋት አግኝቶ ወደ ልማት እንቅስቃሴ እንዲያመራ ከተፈለገ፥ያ ዙሪያውን በጠላት የተከበበ አምባገነን ቡድን ከአካባቢው መወገድ ይኖርበታል። ዛሬ የወያኔ ባለሥልጣኖች በሙሉ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች መሆናቸውን በሚገባ ስለተረዱ፥ እንደቆሰለ አውሬ በምሽጋቸው ውስጥ ገብተው የጭንቅና የፍርሀት ኑሯቸውን ይገፋሉ። መለስ ዜናዊ ፥ ልክ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲኖርበት እንደነበረው ዓይነት ሁኔታ ተጨንቆ ተጠብቦ በከፍተኛ ስጋት ላይ ይኖራል። የሰራትንም  ተግባር ማንም ሳይነግረው እርሱ እራሱ ስለሚያውቃት፥ የሕዝብን አመፅ እየፈራና እየባነነ የምፅኣት ሌሊት ያሳልፋል። በሚኖርበት የቀድሞው የምንሊክና የደርግ ጽሕፈት ቤትን ከኮሎኔል መንግሥቱ በበለጠ መሽጎና አጠናክሮ በሲሚንቶ የግምብ  አጥር ውስጥ ነው ተሸሽጎ የሚኖረው። ዙሪያ ውንም ከራሱ ብሄር ተውጣጥተው በሰለጠኑና በታጠቁ ታማኝ ዘበኞቹ  ሃያአራት ስዓታት ብርቱ ጥበቃ ይደረግለታል። እነኝህ ታማኝ ናቸው የተባለላቸው ዘበኞቹም እርስ በእርሳቸው እንደይተማመኑና እንዳይግባቡ ሆነው ስለተዋቀሩ፥ ትኩረት የሚሰጡት እርስ በእርሳቸው

በመጠባበቅ ስለሆነ፥መለስን ከውጭ ባላንጣ ለመከላከል ያላቸውን አትኩሮት በሁለተኛ ደረጃ ያደርጉታል።ይህ የምሽግ ጥንካሬና የጥብቅ ጥበቃ ሁኔታ በመለስ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሌሎቹም የወያኔ ዋና ዋና በሚባሉት ግለሰቦችም ላይ ይከናወናል። ለምሳሌ በቦሌ አካባቢ የሚኖሩ ቀንደኛ የወያኔ ግለሰቦች ቤቶቻቸው መሳሪያ በታጠቁ ታማኝ ዘበኞች ሃያ አራት ስዓታት ይጠበቃሉ። መቸ እንደሚወጡና መቸስ እንደሚገቡ እንዳይታቅባቸው ብርቱ ጥንቃቄ ለማድረግ ይሞክራሉ። ይህ ግን በሰፈርተኛውና በአካባቢ ነዋሪዎች ዘንድ በትክክል ስለሚታወቅ፥እንዳይታወቁ የሚያደርጉትን ጥረት ሁሉ ብላሽ አድርጎባቸዋል።እነዚህ እንደ ቆሰለ አውሬ ሁል ጊዜ እየባነኑ የሚኖሩ ወያኔዎች፥ዝንተ-ዓለማቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ፈርተውና ጠልተው እስከ መቸ እንደ ሚዘልቁት የተረዱት አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ ከእነርሱ በፊት ከነበረው ከመንግሥቱ ኀይለማርያም የመጨረሻ ሁኔታና ዕድል አለመማራቸው፥ ያስገርማል።

ሕዝብን ጠልቶ፥ዜጎችን ፈርቶ፥ከዜጎች ርቆና ተገልሎ፥ ብሎም በምሽግ ጥንካሬና በመሳሪያ ኀይል  የሰላምና የደህንት ዋስትና የሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ፥ ከኮሎኔል መንግሥቱ የበለጠ በታንክና በስታሊን ኦርጋን የተከበበ  ቡድን አልነበረም። በታማኝ ዘበኝነት ከሆነ ደግሞ፥ በሩሲያና በኪዩባ ባለሞያዎች የሰለጠነና የታጠቀ ነበልባል የሚባል ጦር አልነበረም። ያ ሁሉ ዝግጅትና ድርጅት መንግሥቱን፥ በመጨረሻ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የአመፅ ቁጣ ሊያድነው አልቻለም።  እርሱም ይህችን አውቆ ነው በመጨረሻይቱ ስዓት፥ ከሳሃራ  በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ፥ በሁለንተናዊ መስፈርት ሲለካ ተወዳዳሪ ያልነበረውን የሀገሪቱን የመከላካያ ሠራዊት በትኖና ሀገሪቱንም ለበላዒ- ሰብ አጋፍጦ በጠፍ ጨረቃ የኮበለለው። ይህ አባባል በጣም ጥቂት የሆኑትን ክፍሎች ሊያስከፋቸው ይችል ይሆናል፤ ለሀቀኛ ታሪክና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚታገል ሀገር ወዳድ ድርጅት ግን ለተተኪው ትውልድ የታሪክ ግንዛቤ ለማትረፍ ሲል እውነቱን ከመናገር አይታበይም። ነገሩ፥

"  ኦ ! ኢትዮጵያ ስለ አንች ውነቱን ሳልናገር ብቀር
   ምላሴ ከትናጋየ ተጣብቃ ትቅር።"   ነው።

 የወያኔ መሪዎች አመኑትም አላመኑት፥ወደዱትም ጠሉት፥ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ፥ የተጠሉ፥ የተናቁና፥ የተዋረዱ ናቸው። ይህንንም ሀቅ ሌላው ቢቀር መለስና ግብረ-አበሮቹ ሳይረዱት የሚቀሩ አይሆኑም።ሌላው አጫፋሪው ክፍል ግን የቅቤ እንጎቻ እያነጎተ፥ የሀሰት ስልቻ እየከፈተ፥ የአድር ባይነት ወገቡን እየሰበቀ የእነርሱን በሥልጣን ኮረቻ ላይ መቆየት በእጅጉ  ይፈልገዋል። " ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ" እንዲሉ፥ኢትዮጵያን ለመበዝበዝ

በግድ የነመለስ ዜናዊን መቆየት ይፈልገዋል። በመጨረሻው ሰዓት ግን፥ አጥፊና አስጠፊ፥ አባሪና ተባባሪ፥ብሎም፥ የኢትዮጵያን ጉድጓድ ቆፋሪም ይሁን አስቆፋሪ ተጠቃልሎ የዶግ አመድ ከመሆን የሚያድነው ኀይል አይኖርም። በዓለም ላይ ያሉ ነገሮች፥ ህቆች፥ ኀይሎች ፥ ክስተቶችና ነባራዊ ሁኔታዎች ወዘተ. ሁሉ እንዳልነበሩና እንዳልሆኑ ሆነው ስለሚወገዱ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ያለመኖር አደጋም በቆራጥ ልጆቿ መስዋዕት እንደሚወገድ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

ነገር ግን ሁኔታው እስኪመጣ ከመጠበቅ ይልቅ፥ ሁኔታውን ለመለወጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና በተመቻቹት ሁኔታዎች ላይ ተጠቅሞ ተዓምር መስራትን ይጠይቃል፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ፥ የሚከተሉትን ድርጊቶች በቅድሚያ ማከናወንን ይጠይቃል።

1. የተከበበውን የጠላት ሠራዊት በይበልጥ መቆሚያ መቀመጫ ማሳጣትና ከሁሉቱ ምርጫዎች አንዱን እንዲወስድ ማስገደድና ብሎም፥ከመሸገበት ቦታ አስወጥቶ በሰላም እጁን እንዲሰጥ ማድረግ። ይህም ከብዙ ዕልቂትና ፍጅት ያድነዋል። ይህ መርጫ ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጠውና የሚደገፍም ነው። ያ ካልሆነ፥ ወደ ጠላት ምሽግ ሰብሮ በመግባት የሕዝብን አመፅ አሸናፊነት በተግባር ማሳየት ይሆናል።

2. ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ፥ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን የሚችለው እርሱ እራሱ መሆኑን አምኖ ተቀብሎ፥ የየድርሻውን ማድረግ ወሳኝ መሆኑን ማወቅ አለበት። የራሱን ሀገር ሊያድን የሚችለው እራሱ እንጅ ከእርሱ የበለጠ አንዳችም ኀይል እንደሌለ መገንዘብ፥ የመጀመሪያው ርምጃ እንደሆነ የሁሉም ዜጋ እንጅ የትቂት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች አይደለም። እነ እገሌ ምን እየሰሩ ነው? ማለት፥ በኋላ " በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ" ወደሚለው አንደምታ ያስኬዳል።ይህ ደግሞ ውጤት አያስመጣም።

3. ጊዜው ሲመጣ ወያኔዎቹ እንደ መንግሥቱ ኃይለማርያም ፈርጥጠው ሊሄዱ ይችሉ ይሆናል የሚል ምናልባታዊ መዘናጋትን ከማስተናግድ ይልቅ፥ የተላያዩ ክስተቶች ሊከተሉ ይችላሉ የሚለውን ሁለንተናዊ ትንታኔ ገምግሞና አገናዝቦ ለሚመጡት ክስተቶች አስፈላጊውን መሰናዶ ማዘጋጀት፥ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ቢከሰቱ ከመርበትበት ያድናል። ሌላ ያልተጠበቀ አራተኛ አምባገነን እንዳይመጣ ከአሁኑ ምን ደረግ አለበት? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ጠይቆ መልሱን ከነመፍተሄው ማዘጋጀት በኋላ " ሠርገኛ መጣ ቃሪያ ቀንጥሱ" እንዳይሆን ይረዳል።

በበኩላችን ግን፥ ምንም ይምጣ ምን፥ ከወያኔ ጋር ሳንደራደር ለሕዝባችን በገባነው ቃል-ኪዳን መሠረት መራራውን ትግላችንን እንቀጥላለን!!!!! ፍርዱንም ለታሪክና ለተተኪው ትውልድ እንተወዋለን፡፡